חברת הגיחון בע"מ

ክቡራን ደንበኞች፣

የሃጊሆን ካምፓኒ  የ2019 አጭር ዓመታዊ ሪፖርት ሲያቀርብላችሁ ደስ እያለው ነው፡፡
ሙሉው ሪፖርት በካምፓኒው ድኅረ ገፅ አድራሻ፡ WWW.HAGIHON.CO.IL ላይ ቀርቧል፡፡
የሃጊሆን ካምፓኒ  (በ2001) ዓ.ም በወጣው የውኃ ድርጅት ህግ አንቀፅ 14  ፈቃድ መሠረት የሚሠራ የውኃና የአካባቢው ቆሻሻ አስወጋጅ ድርጅት ነው፤ ድርጅቱ የገንዘብ ወጪን፣ ዕቅድ የማውጣቱን፣ የውኃ አሠራርና ይዘቱን፣ በኢየሩሳሌም፣በመባሠሬት ፅዮንና በአቡ ጉሽ ያለውን ፍሳሽ ውኃን መልሶ ጥቅም ላይ የማዋል ኃላፊነትን ይወስዳል፡፡

የሃጊሆን ካምፓኒ ወደ መዓሌ አዶሚም ያደርሳል፤ ለአዛ ስምጥ ፓለስቴኖችና ራማላ ላሉ ኢንዱስትሪዎች  ውኃ ይሸጣል፤ የሃጊሆን ካምፓኒ ወደ ሚሊዮን የሚጣጉ ነፍሳትን የሚያገለግል ሲሆን ቅርንጫፍ ካምፓኒው ማባጢ ደግሞ የኢየሩሳሌምን፣ ጊብዓት ዘኤቭን፣ የፁር ሃዳሳን፣ የመቫሴሬት ጽዮንን፣ የቢታር ኢሊትን፣ የአዲሱን ጊቭዖን፣ የራማት ራሔልን፣ የቤት ዘይትን፣ የኦራን፣ የሃር ጊሎን፣ የቤቴ ልሔምን፣ የቤት ጀአላን፣ የቢር ኒብዓላ፣ የአራምነ፣ የአልጂብን፣ የመዓሌ አዶምን፣ የሚጽፔ ያሪሆን፣ የክፋር አዶሚምን፣ የዐናቶትን፣ የአዳምንና የአሎንን ውኃ  ያጣራል፡፡

የሃጊሆን ካምፓኒ ልዩ በሆነና በጣም በተሸሻለ Smart Water Utility በሚባል ሞዴል መሠረት ይሠራል፡፡
ይህ ሞዴል ለሃጊሆን ካምፓኒ የሥራ መሥመሩን በማስፋት፣ የቁጥጥር ደረጃን በማሻሻል፣ ካምፓኒው ከሕዝብ ጋር በሚያካሄደው እንቅስቃሴ ሊፈጠሩ ለሚችሉ አለመግባባቶችና ግጭቶች ፈጥኖ መልስ የመስጠት አማራጮችን ያሰፋለታል፡፡

## የውኃ  መዋቅር :

ሃጊሆን GIS(የአካባቢ የመረጃ ሥርዓት) የተባለ በጣም የተሻሻለ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ይሠራል፡፡ ጥበባዊ የውኃ መዋቅርን ለማስተዳደር ለካምፓኒው ልዩ ችሎታን የሚሰጥ፣ የውኃ መስመር የፈነዳበትን ቦታ የሚያሳውቅ፣ ሳይታወቅ ውኃ የሚፈስበትን ቦታ የሚያሳይ፣ የውኃ ጥራት ያለበትን መስመር በማሳወቅና የግፊት መለዋወጥን በመቀነስ የሚረዳ ቴክኖሎጂ ነው፡፡

## የፍሳሽ ኔትዎረክ:

የቤት ፍሳሽን፣ የኢንዱስትሪንና የውኃ ፍጆትን ባጀት ከመቆጠብና ከመሰብሰብ ኃላፊነት በተጨማሪ የውኃ ማስተላለፊያዎችንና ማጣሪያዎችን፣ ወደቦችና ጠልቆ የሚፈሰውን ፈሳሽ ከፍተኛ ጉዳት እንዳይጎዱ ይከላከላል፤ ከኢንዱስተሪዎችና ከልዩ ልዩ ንግዳዊ ተቋማት ምንጭ የሚፈሰውን ፍሳሽ ካምፓኒው ይከለክላል፡፡ መሠረተ ልማቶችን በሰፊው በማሻሻል ካምፓኒው በመቀጠል በከፍተኛ ደረጃ መቋቋም እንዲችልና በከፍተኛ ይዘቱን ከፍ ለማድረግ፣ ይዘቱ ሙያዊ እንዲሆንና የፈሳሽ መዋቅሩ የመደፈን ዕድሉ ዝቅ እንዲል ያደርጋል፡፡

## የልማት ባጀት:

የ2020  ዓመት የልማት ባጀት በግምት ወደ 270 ሚሊዮን ይደርሳል፡፡ ባጀቱ አዳዲስ የውኃና የፍሳሽ መስመሮች እንዲዘረጉ፣ ያሉትን መስመሮች ለማሻሻልና ለመቀየር፣ የውኃ ማጠራቀሚያዎችን ለማቋቋምና ለማሻሻል፣ ለውኃ ፓምፕ ማውጫ ጣቢያዎችና ለውኃ መሣሪያዎችና ለአዳዲስ የቆሻሽ ውኃ ማስተላለፊያዎች ይውላል፡፡ ይህ ባጀት ማኅረሰቡን ቁጥር የመጨምር ሂደትን ለመደገፍ ተብሎ የታቀደ ነው፡፡ እያንዳንዱ ነፍስ ወከፍ የሚጠይቀው፣ የውኃ ጥራትና ማቅረብ ታማኝነት እንደሚያድርግ ይገመታል፡፡ እንዲሁም ባጀቱ ወደ ቄድሮን ሸለቆ የሚፈሰውን ውኃ ለመንከባከብም ተብሎ የታቀደ ነው፡፡

## ፍሳሾችን ማጣራት:

የሃጊሆን ካምፓኒ (95.5%) ባለቤትነቱ (በኢየሩሳሌም ፈሳሾችን የሚያጣራ ድርጅት) በተባለው የማባጢ ካምፓኒ ሲሆን ይህ ካምፓኒ ማቋቋሚያውን፣ ዕቅዱንና የውኃ ማጣራትንና የመንከባከቢያ ወጪን የመሸፈን ኃላፊነትን ይወስዳል፡፡ ውኃን ለማጣራት እኒህ ተቋማት የሚደፉ ፈሳሾችን ለገበሬዎች እርሻ አትክልቶችና ለሕዝብ መናፈሻ የአትክልት ቦታዎችን ማጠጪያ ተስማሚነት ለመለወጥ የሚያስችሉ በጣም በተሸሻሉ ቴክኖሎጂዎችን ይጠቀማሉ፡፡ ከኢየሩሳሌምና ከአካባቢው የላቪያን ሠፈሮች የሚፈሱ ወደ 49 ሚሊዮን ለሚጠጉ ኩብ የውኃ ፈሳሾችን በሦስት የውኃ ማጣሪያ ተቋማትን ይጠቀማል፡፡

ባርኮዱን በመጠቀም"አረንጓዴ ያያሉ" ባርኮዱንቪዲዮኑን እንዲያዩ ተጋብዘዋል

## ሃጊሆን በኔትወርክ(ኢንተርነት):

ለደንበኛ መረጃን በቀላሉ እንዲያገኙና ቶሎ የሚከናወኑትን የካምፓኒውን እንቅስቃሴዎች አገልግሎት ለመቀበል ደንበኛው ምንም መጠበቅ ሳያስፈልገው ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኝ ካምፓኒው መሻሻሎችን ያካሂዳል፡፡ ለ'ግል እንዲመች ተብሎ በተዘጋጀ አካባቢ' የውኃ ወጭ ሂሣብን ለማየትና ለመክፈልም፣ የተዘጋጁ ቅፆችን ለመሙላት ወይም ማውረድ ያስችላል፡፡ መረጃ በሶስት ቋንቋዎች በዕብራይስጥ፣ በአረብኛና በእንግሊዝኛ የቀረበ ሲሆን የማየትና የመስማት ችግር ላላቸውም ተስማሚ ሆኖ በካምፓኒው ድኅረ ገፅ ይገኛል፡፡
በካምፓኒው ድኅረ ገፅ ከአገልግሎት ተወካይ ጋር በሦስቶች  ቋንቋዎች መጻጻፍ(ቻት)፣ የውኃ ጥራት ሪፖርቶችን እስከ ሰባት ዓመት ድረስ ማየትና በየጊዜው የሚከናወኑ የካምፓኒውን የሥራ ቦታ በየጊዜው ማወቅ ይቻላል፡፡

ባርኮዱን በመጠቀም "የመስመር ላይ ቅፅ"ቪዲዮኑን እንዲያዩ ተጋብዘዋል

ወደ ሚቀጥለው ገፅ ይቀጥላል

חברת הגיחון בע"מ

## መልዕክቶችን መላክ(የኤስ ኤም ኤስ):

የሃጊሆን ካምፓኒ በደንበኞቿ ሂሣብ፣ ሆነ ተብሎ ስለሚቋረጥ ውኃ በድምፅና በፅሁፍ መልክት ደንበኞቹን ያስታውቃል፡፡

## አዲሱ የውኃ ደረሰኝ:

ደንበኛው ከአምስቱ ቋንቋዎች በሚስማማውና በሚመርጠው ቋንቋ የውኃ ወጭ ደረሰኝ የሃጊሆን ካምፓኒ ይልክለታል፡፡ በዘመናዊ የእጅ ስልክ አማካይነት በደረሰኙ ላይ ባርኮዱን በማንበብ ወደ ካምፓኒው ድኅረ ገፅ ገብቶ የደረሰኙን ማየትም መክፈልም ይችላል፡፡

ባርኮዱን በመጠቀም "ተለዋዋጭ ሂሣቡን" ቪዲዮኑን እንዲያዩ ተጋብዘዋል፡፡

## የውኃ ክፍያ ደረሰኝ ቀጥታ በኢሜይል:

ፈጣንና ወረቀትን በሚቆጥበው አገልግሎት የውኃ ወጭ የደረሰኝ በኢሜይል ማግኘት ይቻላል፡፡

ባርኮዱን በመጠቀም "የውኃ ወጭ ሂሣብ" ቪዲዮኑን እንዲያዩ ተጋብዘዋል፡፡

## የውኃ ወጭ ሂሣብን በቋሚ በሚወርድ ክፍያ መክፈል፡፡

የውኃ ወጭ ሂሣብን በቋሚ በሚወርድ ክፍያ ለሚከፍሉ ልዩ ጥቅሞች
1. ክፍያውን ለሁለት ዕኩል ክፍሎ(ግማሹን ክፍያ በየወሩ) ያልወለድና ያለ ተጨማሪ ክፍያ መክፈል መቻል፡፡
2. ለደንበኛው የሚመቸውን የክፍያ ጊዜ በወሩ 2፣ 10፣17 ወይም በ24 ቀን እንዲሆን መወሰን፡፡
3. ከተለመደው ክፍያ የተለየ ክፍያ ቢሆን የደንበኛው ሂሣብ እስኪጣራ ድረስ ክፍያው አይከፈልም፤ መልዕክትም ለደንበኛው ይላካል፡፡

ባር ኮዱን በመጠቀም "በቋሚ በሚወርድ ክፍያ" ቪዲዮኑን እንዲያዩ ተጋብዘዋል፡፡

## የታወቀ የውኃ ወጪ ክፍያን ለማወቅ በቤት ያሉትን ነፍሳት ማስተካከል፡፡

በውኃ መዋቅር መመሪያዎች መሠረት የውኃ ወጪ ክፍያ ከተፈለበት ደረሰኝ የተመዘገቡት የቤተሰብ ነፍሳት ብዛት ወይም ከውኃ መቁጠሪያው የሚጠቀሙት ሰዎች ብዛት በቤት ከሚኖሩት ነፍሳት ቁጥር ጋር የሚስማማ መሆኑን እያንዳንዱ ደንበኛ ማረጋገጥ አለበት፡፡ የቤተሰብ ነፍሳት ብዛትን፣ የቤቱን አድራሻ የሚያሳይ የመታወቂያ ወረቀትን አያይዞ በማመልከት ማስተካከል ይቻላል፡፡ በቤት ውስጥ የሚኖሩት አነስተኛው ቁጥር 2 ነፍሳት ናቸው፡፡

ባር ኮዱን በመጠቀም "የቤተሰብ ቁጥር ብዛትን ማስተካከል" ቪዲዮኑን እንዲያዩ ተጋብዘዋል

## የአገልግሎት መረጃዎች:

| ክፍል | በ2019 የአመልካቾች ብዛት | በአማካይ የተጠበቀበት ጊዜ | በህጉ ጸንቶ መገኘት |
|---|---|---|---|
| ለተጠቃሚዎች የስልክ ጥሪ ማዕከል | 229,066 | 97.48%ከ የስልክ ጥሪዎች 81.25% በ40 ሴኮንዶች ውስጥ ተመልሶላቸዋል፡፡ | 100% |
| ተጠቃሚዎች ማጣራት ለሚፈልጉት የፊት ለፊት - የጥሪ ማዕከል | 30,143 | 00:00:51 (51 ሴኮንዶች)<br>ወደ 100% የሚደርሱ ተጠባባቂዎች - 20 ደቂቃዎች በታች | 100% |
| የግብርና የዕዳ ክፍያ የፊት ለፊት - የጥሪ ማዕከል | 5,916 | 00:02:21(ሁለት ደቂቃዎች እና ሃያ አንድ ሰከንዶች)<br>ከተጠባባቂዎች ወደ 97.7% ከ20 ደቂቃዎች በታች ጠብቀዋል፡፡ | 100% |
| የሕዝብ ማመልከቻ | 6,519 | 100% ማመልከቻዎች በ4 ቀናት ውስጥ ተመልሰሶላቸዋል፡፡ | 100% |

ሃጊሆን
ለአንተና ለአገልግሎትህ ቁሟል
ኤሊ ኮሄን ዋና ምክትል አስተዳዳሪ